# መንግሥት ተካፋይ በሚሆንባቸው የፍትሐብሔር ጉዳዮች የንብረት ዕግድ፣ ንብረት ማሰከበርና የውሣኔ አፈፃፀም ስለሚመሩበት ሁኔታ

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች፡-**

ሰለሞን አረዳ

ኃ/ሚካኤል መላኩ

እሸቱ አለነ

መኮንን አንዱአለም

በጃ ታደሰ

አበበ ፊጤ

በቀለ ባሳ

ወርቁ መገርሣ

**በጥናቱ የቀረበ ምክረ ሀሳብ**

1 ከሕጎች ጋር በተያያዘ እየታዩ ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ ሕጎችን በተለይም የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉን በማሻሻል ግልፅ ያልሆኑ ድንጋጌዎችን ግልጽ ማድረግ አዳዲስ ሁኔታዎችን ማካተት እና አላስፈላጊ የሆኑትን ማስቀረት፣

2 መንግስት ተካፋይ በሚሆንባቸው የፍትሐብሔር ጉዳዮች ክስ ከመቅረቡ በፊት ወደፊት ተከሳሽ የሚሆነው ሰው ወይም ሰዎች ንብረት ሊታገድ ወይም ሊከበር የሚችልበትን አሠራር መዘርጋት። የንብረት ዕግድ ወይም ማስከበር ትዕዛዝ ጉዳዩን አከራክሮ ውሳኔ በሚሰጠው አካል የሚሰጥ ሆኖ ዕግዱ ወይም ማስከበሩ የሚቆየውም እንደ ጉዳዩ ሁኔታ እየታየ ከአሥራ አምስት ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ይሆናል። ይህም ጊዜ የሚራዘም አይሆንም።

3 ጉዳዩ የሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች የንብረት ዕግድና ንብረት ማስከበር ጥያቄ በወቅቱ እንዲያቀርቡና ትዕዛዝ የሚሰጠው አካልም በግባቡ እንዲሰጥ ሊያደርጉ የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

4 ማንኛውም ሰው ክስ የሚቀርብበት ወይም የቀረበበት መሆኑ አውቆ ንብረቱን በማሸሽ ሀሣብ ከዕዳ ለማምለጥ ለሌላ ሰው አስተላልፎ ከሆነና ሦስተኛ ወገንም ይህንን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ንብረቱን በግዥ ወይም በሌላ መንገድ የወሰደ ከሆነ ውሉ በህግ ተቀባይነት እንዳይኖረው የሚያደርግ አሠራር በሥራ ላይ ማዋል፣

5 የአፈፃፀም ሂደት ሊወስድ የሚገባውን ጊዜ መወሰን፣

6 የፍርድ ባለዕዳዎች የንብረታቸውን ዝርዝር ለውሣኔ አስፈፃሚው እንዲያቀርቡ እና የተሳሳተ መረጃ የሚሰጡትን በወንጀል ተጠያቂ እንዲሆኑ የሚያደርግ ግልፅ አሠራር መዘርጋት፣

7 መንግስት ተከፋይ የሚሆንባቸው የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች በድርድር ጭምር የሚያልቁበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

8 በመንግስት አካላት መካከል የሚነሱ ክርክሮች ወደ ፍርድ ቤት መሄድ ሳያስፈልጋቸው በአስተዳደራዊ መንገድ እንዲፈቱ ማድረግ፣

9 ዘመናዊ የንብረት ምዝገባና መረጃ ሥርጭት ሥርዓት መዘርጋት፣

10 የፍትሐብሔር ውሳኔዎችን የሚያስፈጽም በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ቁጥጥር የሚደረግበት እራሱን የቻለ ጽህፈት ቤት ማቋቋምና ለመንግስት የተሰጡ ውሳኔዎችን የሚያስፈጽሙ የተለዩ ባሙያዎችን መመደብ፣ እንዲሁም ደረጃ በደረጃ ሥራው በግል ድርጅቶች ጭምር የሚሰራበትን ሁኔታ ማመቻቸት

11 ለውሣኔ አፈፃፀም ተግባር በሀራጅ የሚሸጡ ንብረቶች ትክክለኛ ዋጋቸውን እንዲያወጡ ለማድረግ የሀራጅ ማስታወቂያዎችን ለህብረተሰቡ በስፋት በማሰራጨት የገዥዎችን ቁጥር ማብዛት፣ በሽያጩ ሂደት ላይ መሰናክል በሚፈጥሩ ግለሰቦች ላይ ጥብቅ እርምጃ መውሰድ፣

12 በዘርፉ ለተሰማሩ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የመንግስትንና ሕዝብን ጥቅም አጠባበቅና በአጠቃላይ የሕጎችን አፈፃፀም በሚመለከት ተከታታይ ስልጠና መስጠትና የእርስ በርስ መማማሪያ መድረክ ማመቻቸት፣

13 የሕብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ ሕግ የመፈጸም ባሕልን ማዳበር፣

14 በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎችን ተነሳሽነት ለማሳደግ የሚያስችል የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት፣

15 የፍትሕ ተቋማትንና አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችን በሰለጠነ የሰው ሀይል፣ በጀትና ቁሳቁስ ማጠናከር፣ አሠራራቸውን ዘመናዊ ማድረግና ኃላፊነታቸውን በብቃት ሊወጡ በሚችሉበት መንገድ ማደራጀት፣

16 በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሙያዎች ጥብቅ የሥነ ምግባር ደንብ ማውጣት፣ የግልፅነትና ተጠያቂነት አሠራርን ማጠናከር፣ ውጤታማ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት፣ የሥነ ምግባር ግንዛቤአቸውን ማሳደግና ሙስና በሚፈጽሙት ላይ ጥብቅ እርምጃ መውሰድ፣